# ስማችን --- ኢወክንድ
# ልሳናችን ------ ነቅንቅ

ቅፅ 1 ቁጥር 1 ኅዳር 2002 ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ መብትና ጥቅም እንደራደረም ብለው የተሠዉ ታላላቆቻችን እምቢኝ ለኢትዮጵያን ፈክረው ያለፉ አባት እናቶቻችን፣ አያት ቅድመ አያቶቻችን ዛሬ በእኛ ዘመን የደረሰ ውን ቢሰሙ ምን ይሉ ይሆን? የሚል ጥያቄ ተነስቷል።

የገናና ታሪክ ባለቤት ኢትዮጵያ የፈጠረችን ልጆቿ ምን ተነካን? የሚል ጥያቄ ተጭሯል።
ከወጣቱ ለወጣቱ--መልዕክት ይተላላፍ ---

የአደንቁረህ ግዛው ወያኔያዊ ፖሊሲ ሰለባዎች የሆንን ወጣቶች ሰብረነው የወጣነውን የዘረኝነትን አሽከላ ዳግም ላንገባበት እርግጠኞች ነን። ባለፉት 18 የጨለማ ዓመታት ውስጥ ደቀን ያደግነው ወጣቶች በተስፋና በዕምነት በታጠረ ጧፍ ተፈላልገን ከተደራጀን እነሆ መንፈቃችን መጥቷል። በ6 ወር ጉዟችን ሰፍተናል፣ በቁጥርም በርክተናል፣ ድርጅታዊ ሥራችን--ዕድሜ ለቀደምቶቻችን እያልን -- በደማቸው ባስተማሩን ህቡዓዊ አሰራር አድማሳችን ሰፍቷል። ዛሬ ስንጮህ ላንሰማ፣ ብንነርት የማናደቅ ሆነን ልንታይ እንችላለን። ነገ ደግሞ ዚቁ ሲቀየር የስያሚያችን ኢወክንድነት የኢትዮጵያ አለኝታ ክንድነትን እንደሚያስመሰክር ላፍታ ጥርጣሬ አይገባብንም።

ዛሬ የቆመንበትን ዙሪያ ገባውን ስንፈትሽ፣ ጓዳ ጉድጓዳውን ስንቃኝ እመ ኢትዮጵያና ሕዝቧ የሲቃ ደወላቸው የሰቆቃ ጩኸታቸው ወክንድ ወክንድ የሚል ትርጓሜ ይሰጠዋል። ዕውነትም ተፈረጠመ የወጣት ክንድ ዛሬ ነው መፈክሩ።

> በአደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ጎንደር የተጨፈጨፉ ስጋዎቻችንን በደማቸው የተለቃለቀው ወያኔ፣
> በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ ገብቶ ያረደው ወያኔ
> በወጣት ተማሪ ጓደኞቻችን ደም የረሰረሰው ወያኔ
> ወጣት እህቶቻችንን ያለርህራሄ ለባህር ማዶ የሸጠው ወያኔ
> የአዋሳ ወጣት አርሶ አደሮችን በጥይት አረር የለበለበው ወያኔ
> የኢሉባቦር ልጆችን እንደ ድኩላ አድኖ የጨረሰ ወያኔ
> የኢትዮጵያ የምዕራብ በረኞችን የጋምቤላ ልጆችን ዘር ያጠፋ ወያኔ
> የሀገሪቷን ሀብት ቀምቶ የደለበ ወያኔ
> አርሶ አደሩን በግዳጅ ያፈናቀለው ወያኔ

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

ባልተመረመረ መርዝ ማዳበሪያ መሬታችንን ያመከነ ወያኔ

የአዲስ አበባን ነዋሪ በልማት ስም የወረሰው ወያኔ

ዘረኝነትን አስፋፍቶ እርስ በርስ ያጫረሰው ወያኔ

የእኛ ወጣቶችን በውሸት ትምህርት ፖሊሲ ያደናቆረ ወያኔ

እነ ሽብሬ ደሳለኝን የበላ ወያኔ

15 ሺ ወጣት እስረኞችን በጭካኔ እያሰቃየ ያለ ወያኔ

የዴሞክራሲ ቀንዲል ለኳሾችን እነ ፀጋዬና ይስሀቅን አፍኖ ያጠፋ ወያኔ

በአጠቃላይ ምስጢረ ኢትዮጵያን ያረከሰ ሰይጣናዊ ሥርዓት ዛሬ ደግሞ ብዙ ሚሊዮን ሄክታር ድንግል መሬታችንን ያለ ይሉኝታ ለባዕዳን በሽያጭ ሲያስረክብ እኛ ወጣቶች የምንሰጠው ምላሽና የምናስተላልፈው፥ በከርሰ መቃብራችን ላይ እንጂ በውናችንስ አይሆንም ነው መልዕክቱ፤ አይሞከርም ይሆናል ምላሻችን። ከ80 ሚሊዮን ሕዝብ የተፈጠርን ነንና በብሶቱ የተወለድን ኢ.ወክንድ ነንና፤ በክንዳችን ኢትዮጵያችን ማዕረጓን እናስመልሳለን ነው የፈረጠመው ውሳኔያችን !

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ፤

የኢሕአፓ ወጣቶች ክንድ ድርጅት ኢ.ወክንድ ሩቅ አሳቢ ግን ቅርብ አዳሪነትን ከኢሕአፓ ታላቆቻችን አልወረስንምና ከወሬው ቀንሰን፤ ከሥራው ደጉሰን ለመገኘትና ቅድስት ኢትዮጵያን ከርኩሳን ለማላቀቅ ተደራጅተን ማድቀቅ ነውና ራዕያችን፤ ወጣቶች በያላችሁበት እየተደራጃችሁ ለማይቀረው ፍልሚያ በተጠንቀቅ ተዘጋጁ ይሆናል የዛሬው መልዕክታችን።

አፄ ቴዎድሮስ በፍቅሯ ከንፎ ጥይት የጠጣላት ኢትዮጵያ፤

አፄ ምኒሊክ በእምነቱ እቴጌ ጣይቱ ብጡል በብልሀቷ ጠላቷን የመቱላት ኢትዮጵያ

እስላም ከክርስቲያኑ የተዋሀደላት እናት ኢትዮጵያ፤

ሺህዎች አፍላ ዴሞክራሲያውያን የተሰዉላት ኢትዮጵያችንን ወደ ክብሯ ከፍ ለማድረግ የወጣቱ አስተዋፅዖ አይነተኛ መሳሪያ መሆኑን ተረድተን፤ ካለእኛም ካለ ልጆቿ በስተቀር አጋር አልባ የሆነችው ሀገራችን ከውስጥና ከውጭ ቅኝ ገዢዎች ለመላቀቅ የማትችል መሆኗን ተገንዝበን በያለ ንበት ትግሉን እናፋፍም ነው የዛሬው የኢ.ወክንድ ጥሪ።

መለስ ዜናዊና ኩባንያው ሀገራችንን ለህንድ፤ ለቻይና፤ ለአረቦቸና ለሌላም ሌላም ሽጦ ለመጥፋት የሚያደርገው የጣር መወራጨት ኢትዮጵያዊ ክብራችንን ገሽልጦታልና ግጦ ሳይጨርሰን ይህን ሥርዓት ለመገርሰስ ክንዳችንን እናጣምር እያለ ኢ. ወክንድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

የኢትዮጵያን ድንግል መሬትንና የኢትዮጵያ አርሶ አደር መብትን በትግል እናስከብራለን!!!

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com